# የህብረቱ ሂደትና የውህደት ጥያቄ

ባለፉት አስር የኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት ፈጠርን ሲሉ አንዴም ሁለቴም ተደምጠዋል። ህብረቶቹ የቀየሱት ግብ ተግባር ላይ ሲውል ግን አልታየም ። ይህ ሁኔታ የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ልብ እንዳቆሰለ የማይታበል ሃቅ ነው ። ችግሩ የት ላይ እንደሆነ ተከታትሎ ማወቅና መፍትሔው መሻት የሁሉም ሃገር ወዳድ ዴሞክራት ሃላፊነት ቢሆንም ለህዝብ ቁመናል የሚሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በቅድሚያ ይመለከታቸዋል ።

ድርጅቶቹ ይህ ከባድ ሃላፊነት በቅድሚያ እንደሚመለከታቸው ባይስቱትም በመካከላቸው ያለው የመከፋፈልና የመጠላለፍ ሁኔታ ሲታይ የኢህአዴግ መሪዎች የቀየሱት የከፋፍለህ ግዛ ፈሊጥ እየተሳካ ነው ለማለት ያስደፍራል ። ከፖለቲካ ትግሉ ብሁ ያልራቁት የሲቪክ ድርጅቶችም በዚሁ የመከፋፈል ግብግብ አሉበት ። ይህንኑ ሁኔታ የሚያረካቸው አምባገነኖቹ የኢህአዴግ መሪዎች « ጠንካራ ተቃዋሚ አጣን » እያሉ ያፌዛሉ ። በዚህ ማኸል ሀገራችን ከችግር ወደ ከፋ ችግር እየሰጠመች ፣ ህዝባችን ከድህነትና በሽታ ወደ ከፋ ውድቀት እየወረደ አሳፋሪ ሁኔታ ላይ እንዲገኝ አድርጎታል ።

ሀገራችንና ህዝቦቻችን ለሚገኙበት አስከፊና አሳፋሪ አንዳንዴም ዘግናኝ ሁኔታ ተጠያቂዎች ከሥልጣን በስተቀር የሀገሪቱ የአሁኑ ይሁን የመጭው ዕድል የማይታያቸው የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ሲሆኑ፣ ይህን አስከፊና አደገኛ ሁኔታ ለመለወጥ ነጋ ጠባ ቃል የሚገቡት የተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎችም ተደጋግፈው በህዝቡ የሚጠበቀው ለውጥ አለማምጣታቸው ብቻ ሳይሆን አምባገነኖቹ በሚፈልጉት የመከፋፈል ትርምስ ውስጥ በመግባታቸው ከተጠያቂነት አያመልጡም ። ለምን ከተጠያቂነት እንደማያመልጡም ሌሎች አሳሳቢ ጥያቄዎችን አክለን እንደሚቀጥለው እናየዋለን ።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት ፈጥርን ሲሉ እንጂ ለውጥ ሲያመጡ አይታዩም ። ለምን ? ለውጥ ለማምጣት ካለመቻላቸው በተጨማሪ እርስበርሳቸውም ሲጠላለፉ ይታያሉ ። ለምን? ህብረቱ እንዲሰምር ምን መደረግ አለበት? ከህብረት ባሻገር ውህደት ማምጣት ይቻላልን ?

እነዚህ ጥያቄዎች ለወገኑ የሚያስብ ኢትዮጵያዊን የሚያስጨንቁ ቢሆኑም ተገቢውን ምላሽ አላገኙም። ይመለከቱኛል የሚል ሁሉ መልስ ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ መልስ ሊሰጥበት ይገባል ። በበኩላችን በተግባር የሚሸኝ አመለካከታችንን ቀጥለን እናቀርባለን ።

ለምክክራችን ይረዳ ዘንድ በቅድሚያ ህብረትና ውህደት የሚሉ በዚህ ጽሑፍ የሚነሱ ቁልፍ ሀሳቦች ከፖለቲካ ጠቅሜታቸው አንጻር ባጭሩም ቢሆን እናብራራ ።

## ህብረት

ከፖለቲካው አቅጣጫ ሲታይ ህብረት የተለያየ ዓላማና ዕቅድ (ፕሮግራም) ያላቸው ኃይሎች ይህንኑ ልዩነታቸውን ለማስተናገድ የሚያስችላቸው ሥርዓት ለመፍጠር በጋራ ተልመው የሚንቀሳቀሱበት የሰፊ ዓላማ ስብስብ ነው ።ህብረት ግልጽ መቻቻልን-ሰጥቶ መቀበልን (compromise) የግድ ይላል ። ያንዱን ወገን የበላይነት የሚያስተናግድ ህብረት ውጤት እንደማይኖረው መታወቅ አለበት ። የህብረቱ አባል ድርጅቶች የየግል ድርጅቶቻቸው ሥራዎችን ለይተው የሚያካሂዱበት ሥርዓትና ሥነ-ምግባር ግልጽ አድርጎ ይቀበላል ።

<u>ለምሳሌ</u> ስምንት ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች በ1998 ዓ ም ፈ ፓሪስ ላይ ተገናኝተው በኢትዮጵያ ሁሉም ፖለቲካዊ ድርጅቶች እንደየእምነታቸው በነፃ የሚንቀሳቀሱበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመፍጠር ተሰማምተው የፈጠሩት ድርጅት (ኢተፖድህ) ህብረት ነው ።እያንዳንዱ ድርጅት ኢህአዴግ በዘረጋው አምባገነናዊ ሥርዓት ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንደተረገጡና ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ መታገል እንደሚያስፈልግ አቋሙ ነው ።

## ውህደት

በመሠረታዊ ፖለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የዓላማና የዕቅድ ተመሳሳይነት ያላቸው የተለያዩ ድርጅቶች አንድ አጠቃላይ ድርጅት ፈጥረው ለአንድ የጋራ ዓላማ የሚቆሙበት ዘላቂ ድርጅት የሚፈጠርበት ሂደት ነው ። ውህደት የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማና ሥነ-ምግባር ይዘትም ያጠቃልላል ። ውህደት የፈጠሩ ድርጅቶች በድሮው ድርጅታቸው ስም መንቀሳቀስ አይችሉም ። ስለዚህ የድሮው ድርጅት ህልውና በአዲሱ የተወሀደ ድርጅት ስምና ህልውና ይጠቃለላል ማለት ነው ።
<u>ለምሳሌ</u> ከ8ቱ የኢተፖድህ አባል ድርጅቶች 3ቱ ውይም 5ቱ ወይም በሙሉ ዓላማቸውና ዕቅዳቸው አንድ አድርገው በአንድ ድርጅት ሥር ቢጠቃለሉ ውህደት ፈጠሩ ማለት ነው ። ሰዎች በአንድ ድርጅት ሥር እንደሚሰማሩት ሁሉ ድርጅቶችም እንደዚሁ ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

ቀጥለን እንግዲህ ከፖለቲካ ድርጅቶች እንቅስቃሴ በተዛመደ መልኩ በህብረትና በውህደት ዙርያ የተነሱትን ጥያቄዎች እንመልከት ።

ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ከ1991 ዓ.ም.ፈ ጀምሮ በአገር ቤት መንቀሳቀሻ ዴሞክራሲያዊ መድረክ ሊያገኙ ያልቻሉት ድርጅቶች በየወቅቱ እየተሰባሰቡ ህብረት እየፈጠሩ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚፈጠርበት ሁኔታ ለማመቻቸት እየታገሉ መሆናቸው ለማንም ኢትዮጵያዊ ግልጽ ነው ። አገር ቤት ውስጥ ከሚደረገው ትግል ጋር ለማቀናጀትም ብዙ ጥረዋል ። ይሁን እንጂ በህብረቱ አፈጣጠር ላይ ይሁን ከህብረቱ ማግስት በሚከሰቱ ችግሮች ህብረቱ የሚጠበቅበትን ግብ ሊመታ አልቻለም ። ይህ ሁኔታ የብዙ ሀገርና ህዝብ ወዳድ ኢትዮጵያዊ ልብ ሳያቆስል አልቀረም። ለዚህ የዳረገን ችግር ምንድነው? መፍትሔው ስ ምን መሆን አለበት?

ከህብረት አጀማመር ስንነሳ አንድ ትልቅ በሽታ እንዳለ ይታያል ። እሱም ህብረት የሚመዘነው በይዘቱ መሆኑ ይቀርና በህብረቱ አነሳሾች ወይም ደግሞ የተጀመረው ህብረት እንዲያስተባብሩ በሚመረጡ ሰዎች ላይ ወደ ማትኩር ይሆናል ። ማንም ያነሳሳው ማንም ፤ ህብረት ከተባለ የተለያዩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ቅንብር እንጂ የአንድ ሰው ውይም ድርጅት አይደለም ፤ ሊሆንም አይችልም ። የአንድ ሰው ወይም ድርጅት ዓላማም ይሁን የበላይነት ለማስተጋባትም ፍጹም አይችልም ። አለዛ ህብረት መሆኑ ወዲያው ያከትማል ።

ስለዚህ ህብረት ፈላጊ ሁሉ ከዚህ መርህ ካልተነሳና ለተግባራዊነቱ ካልተንቀሳቀሰ ህብረት ፈላጊ ነኝ ቢል ራሱን እያሞኘና ህዝቡንም እያመሰ ነው ። ከዛም አልፎ የህብረትን አስፈላጊነት በውል ተረድተው ለሚታገሉ ኃይሎች እንቅፋት መሆን ነው ። ከዚህ አንጻር ሲታይ በዚህ ሁኔታ ህብረት አይቻልም ብለው ራሳቸውን ያገለሉ ድርጅቶች ፤ መስለው በመቀላቀል አለመበጥበጣቸው ሳያስመሰግናቸው አይቀርም ። በተለይ ህብረቱን የሚቃወሙበት አቋም በግልጽ አስቀምጠው ይፋ አድርገው ቢሆን ኖሮ ሌላው ሊማርበትና ሊደግፈው ወይም ሌላ መውጫ ሊያይ ስለሚችል ቁርጠኛ አቋም በተሰኘላቸው ።

ህብረት ወደ ፈጠሩት ስናተኩር ፤ ብዙ ገንዘብና ጉልበት ፈሶበት ፤ አያሌ ውይይት ተካሂዶበት በስምምነት የተፈጠረው ህብረት በሂደት እየጠነከረ የማይሄድበት ምክንያት ምንድነው? የዚህ ችግር መንስ ኤ አሁንም ህብረቱን ከፈጠሩት አባል ድርጅቶች የሚርቅ አይደለም ። በዚሁ ሰበብ በተከታታይ የተንጸባ ረቀ -ድክመቶች እንጠቁም ።

ሀ - ህብረቱ የነደፈው አቋምና አሠራር ወደ ጎን በመተው የራስ ድርጅትን አቋምና አሠራር ወደ ማጉላት ማዘንበል ፤ በሰበቡም የራስ ድርጅትን ልዕልና ወይም ታዋቂነት መሻት ፤

ለ - በህብረቱ ውስጥ በውይይት ወይም በህገ - ደንባዊ አሠራር ሊፈቱ የሚችሉትን ችግሮች ሊፈቱ እንደማይችሉ አድርጎ በማቅረብ ህብረቱን የሚያዳክም ቅስቀሳ ማካሄድ ፤

ሐ - ፀረ -ህብረት የሚል ቅጽል እንዳይለጠፍባቸው ወይም ከህብረቱ የሚያርቃቸው ምክንያት በውል ማቅረብ ባለመቻላቸው ወይም ባለመፈለጋቸው ብቻ በህብረቱ ውስጥ መገኘት ፤

መ - ህብረቱ ምናልባት ከተሳካለትና ለስልጣን ከበቃ በሥልጣን ክፍፍል ድርሻ ይኖረናል ከሚል በመነሳሳትም በህብረቱ አለሁ ለማለት እንጂ ህብረቱ የሚጠይቀውን መስዋእትነት ለመክፈል አለመዘጋጀት ከሚታዩ ጉድለቶች ከፊሎቹ ናቸው ።

እነዚህ ከፊል ድክመቶች በተፈጠሩት ህብረቶች ላይ ያደረሱትን ተጨባጭ ተጽእኖ (መሰናክል) አንድ - ሁለት ተመኩሮዎችን በማንሳት መመልከት ለግንዛቤ ይረዳል ።

## ተመኩሮዎች

ከ1991 ዓ.ም.ፈ ጀምሮ ብዙ የህብረት ሙከራዎች ታይቷል ። ይሁን እንጂ አንዱም ተፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት አልበቃም ። ቀጥለን በተከታታይ ብቅ ያሉትን የፓሪስ - 1 ና 2 ህብረቶች ልምድ እንመልከት ።

ፓሪስ - 1 1993 ዓ.ም.ፈ 8 ድርጅቶች (ኦነግን ጨምሮ) ፓሪስ ላይ ተገናኝተው በሰላምና ዕርቅ መርህ ላይ በመመሥረት ህብረት ፈጠሩ ። ዓላማው በሰላም መንገድ ኢህአዴግ የዴሞክራሲ ሂደት እንዲቀበልና ማንም ኢትዮጵያዊ ፖለቲካዊ ድርጅት አገሩ ውስጥ ገብቶ ያለምንም ተፅእኖ ህዝቡን እንዲያደራጅና የአብዛኛው ህዝብ ፍላጎትና ውሳኔ በተግባር እንዲተረጉም ለማስቻል ነበር ። ኢህአዴግ በዚህ ሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ከተጓዝኩ ከሥልጣን እባረራለሁ የሚል ስጋት ስለገባበት ጥሪውን አልተቀበለውም ። የህብረት ጅምሩንም በዚህ ደካማ እምነቱ አጨናገፈው ። ለሰላምና ዕርቅ ኮንፈረንስ አዲስ አበባ ሊሰበሰቡ የተላኩት የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችንም ከአየር ማረፍያ እየተቀበለ እስርቤት ውስጥ አጉራቸው ። የታቀደው ስብሰባ በተወሰኑ ድርጅቶች ተካሂዶ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ቢፈጠርም መሠረታዊ ለውጥ የሚጠይቁ ድርጅቶች ከመሳተፍ ስለታገዱ የተፈለገውን ለውጥ ሊያመጣ የሚችል አልሆነም ።

በተቃዋሚ ድርጅቶች በኩልም ድክመት አልጠፋም ። አዲስ አበባ ውስጥ ስብሰባ ሲታቀድ ብዙ ጥያቄዎች ተነስተው ሳይታሰብባቸው በችኮልላ ተዘለዋል ። አንደኛና ዋናው ኢህአዴግ አምባገነን ድርጅት እንደመሆኑ መጠን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ከተወዳደረ ሥልጣን እንደሚያጣ አበክሮ ስለሚያውቅ ይህንን ስብሰባ እንደሚያጨናግፍ መገንዘብ ነበረበት ። ይህንን እንቅፋት ለመከላከል ፤

ሀ/ የህብረቱ መቀናጀት በቅድሚያ እንዲጠናከር ፤

ለ/ ከስብሰባው ባሻገር ምን ምን መደረግ እንደሚኖርበት ለህዝቡና ለድርጅቶቹ በመንደርደርያነት ግልጽ እንዲደረግ ፤

ሐ/ ህዝባችንና ዓለም አቀፍ ህብረተሰብ በጎናችን ተሰልፎ በኢህአዴግ ላይ ተፅዕኖ እንዲፈጥር አስቀድሞ እንቅስቃሴ ይደረግ የሚሉ ሀሳቦች ቀርበው ተረግጠው ታለፉ ።

ለምን ተረግጠው ታለፉ ብሎ መጠየቅ አገባብ ይሆናል ።
ከላይ የተጠቀሱት አሳሳቢ ጥያቄዎች ቸል በማለት ወደ አዲስ አበባ የተራመዱት ድርጅቶች በወቅቱ

የነበረው የህዝቡ መነሳሳት ተገን በማድረግ ኢህአዴግን አውርደው ሥልጣን ለመያዝ የሚቻል ስለመሰላቸው ነበር ። ሌላ ምክንያት ይኖረዋል የሚል እምነት የለንም ። ይህንን ትዝብት የሚያጠናክር ነጥብም አለ። ይኸውም ምናልባት ኢህአዴግ ይህንን ስብሰባ ሊያጨናግፍ ስለሚችል ስብሰባው እንዳይተጓጉል ከኢትዮጵያ ውጭም ሌላ የመሰብሰቢያ ቦታ ግምት ውስጥ አስገብተን እንዘጋጅ የሚል ሓሳብ በተደጋጋሚ ቀርቦ እነዚሁ ድርጅቶች በተጠቀሰው አቅጣጫ ብቻ ስለተቃኙ ይህን ተጠባባቂ ዕቅድ አልደገፉትም ። ቅንጣት ታክል ትኩረትም አልሰጡትም ።

አንድ ዓመት ሙሉ የተደከመበት 300 ሺ ፍራንክ የፈሰሰበት አያሌ ኢትዮጵያዊ ተነሳስቶ ተስፋ ያደረገበት የህብረት እርምጃ ተሰናከለ ።

ዴሞክራሲ አንሰራፍቶ ፈተና ውስጥ እንዳይገባ የፈራው ኢህአዴግ በፈጠረው መሰናክልና የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች የኢህአዴግ ፖለቲካዊ ተፈጥሮ በሚገባ ገምግመው ተገቢውን ዝግጅትና እርምጃ ባለመውሰዳቸው የፓሪስ-1 ውጥን (ሰላምና እርቅ በኢትዮጵያ) ተኮላሸ ። ህብረቱም ደበዘዘ ። በዚህ ሁኔታ የተፈጠረው አማራጭ ኃይሎች ም/ቤትም ስም ከብዶበት ሽባ ሆኖ ቀረ ።

ከሶስት ዓመታት በኋላ የካቲት 3 ና 4 1996 ዓ.ም.ፈ የሰላምና ዕርቅ በኢትዮጵያ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዳዲስ ለንደን ላይ ተገናኝቶ ያለፈበት የሥራ ሂደትን ሲገመግም ከላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች በዝርዝር ተወያይቶባቸዋል ። ለሌላ የተጠናከረ የህብረት ጅምርም (ፓሪስ-2) መንገድ ጠርጓል ።

<u>ፓሪስ-2</u> ሰላምና ዕርቅ በኢትዮጵያ (ፓሪስ-1)ን የወጠኑት ድርጅቶች (በገዛ ፈቃዱ የቀረው ኦነግን ሳይጨምር ) እንደገና ፓሪስ ላይ መስከረም 1998 ዓ.ም.ፈ ተሰብስበው ኢተፖድህ የተሰኘው ህብረት መሠረቱ ። ከሰፊ ውይይት በኋላ ፤

ሀ/ የዴሞክራሲ ሂደትና የነጻ ምርጫ ትልም ፤

ለ/ የብሔራዊ ውይይት አስፈላጊነት በሚሉ ርእሶች ፤ ሰላምና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ የሚሰፍንበት አቅጣጫ በዝርዝር ተወያይቶ የትግል አቅጣጫ ቀየሰ ። ትልሙና ውሳኔዎቹ ያኔም ሆነ ወደፊት የተዋጣላቸው አቋሞች እንዲሆኑ በጥልቀት ተወያይቶ አሰፈረ ።

ይሁን እንጂ አባል ድርጅቶቹ ባረቀቁትና ባጸደቁት የትግል መመርያ ጸንተው ወደግቡ የመገስገሱ ሁኔታ ላይ በሚጠበቀው መንገድ መጓዝ አልቻሉም ። ምክንያቱስ ?

ዋናው የሀገራችን የወደፊት ዕድል (የሰላምና የዴሞክራሲ አቅጣጫ የመያዝ ጉዳይ) በዚህ ጥያቄ ዙርያ ላይ ይሽከረከራል ። የኢህአዴግ አመራር በሰላም በዴሞክራሲ ለህዝበ-ውሳኔ በሩን ይከፍታል ብሎ ማሰብ የዋህነት አለያም አድርባይነት ከመሆን አያልፍም ። ያው የተያያዘው የምርጫ ትያትር ግን በእርግጥ ይቀጥልበታል ።

እንግዲህ ምክንያት ወደ ተጠየቀበት ጉዳይ እንመለስ ። ይኸውም የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ባረቀቁት የትግል መመሪያ ፀንተው ተባብረው ለውጥ ለምን አያመጡም የሚለው ሲሆን 4 ወይም 5 አጠቃላይ ምክንያቶች መስጠት ይቻላል ።

1. የህብረት አስፈላጊነት ወይም ደግሞ ምንነቱን በሚገባ ለመገንዘብ የሚያስችል ፖለቲካዊ ባህል ያልዳበረ በመሆኑ ነው ። ህብረት ለጋራ ድል ሲባል መቻቻል እንደሚጠይቅ ቢያምኑም በቃል እንጂ በተግባር የማይቀበሉ ድርጅቶች አሉ ። በህብረቱ ጉባኤና መደበኛ ስብሰባ ውስጥ አብጠርጥረው ተከራክረው ያጸደቁትን መመሪያ ከስብሰባው ሲወጡ መናድ ይጀምራል ። አንዳንዶቹ ለአባሎቻቸውና ለህዝብ ያስተጋቡትን አቋም በህብረት ከተቀበሉት አቋም ጋር የማይጣጣም ይሆንና በህብረቱ መቋቋም ምንም ለውጥ እንዳልተደረገ ለማንጸባረቅ ብዙ ይዘባርቃሉ ። ሌሎቹ ደግሞ ድርጅታቸው በህብረቱ አመራር ውስጥ የበላይነቱን ስላልጨበጠ "እነዚያ" ከመሩት ህብረቱ አይሳካም ብለው ይቀሰቅሳሉ ። እኛ ካልመራነው የትም አይደርስም ለማለት ነው ። በግል የሚጠሉትን ወይም የሚፈሩትን ድርጅትና ማህበር በህብረቱ እንዳይሳተፍ ሰንካላ ምክንያት የሚሸርቡም አልጠፉም ። በዚህ ዓይነት ጉዞ ስለሄዱ የህብረት ትግሉ ተሸረሸረ ፤ ተናደ ፤ መጠላለፍም ቀጠለ ። ከዚህ መጠላለፍ ያተረፈ ቢኖር የኢህአዴግ አመራር ብቻ እንደሆነ ግን መዘንጋት የለበትም ። ኢህአዴግ የሚፈልገው የተቃዋሚው ጎራ መዳከምና የህዝቡ መከፋፈል ያለ ብዙ ጥረት ተግባር ላይ ውሎለታል ።

2. በህብረቱ ፀንቶ ትግሉ የሚጠይቀውን ከበድ ፈተና እየተወጡ አለመዝለቅ ይታያል ። አንዳንዱ ድርጅት በህብረቱ መመሥረት ያመነበትን አቋምና የገባውን ቃል ረግጦ ፤ ጠላት ብሎ ከፈረጀው ኢህአዴግ ጋር ህብረቱ በሚንድ መልኩ ግልጽና ህቡዕ ግንኙነት ለመፍጠር ይቧዝናል ። በህብረቱ መሳተፍ ይሁን ከህብረቱ መሰናበት መብቱ ሆኖ እያለ ህብረቱን እንዲመሠርት ያስገደዱት ሁኔታዎች ሳይለወጡ በጎን ህብረቱን የሚሸረሽሩ ተግባሮች ያካሂዳል ። ይህ ዓይነቱ ክንዋኔ ሲታይ ክህደትም ፤ አቋመ-
ቢስነትም ከመሆኑ ባሻገር ድሮውኑ ለምን ህብረት እንደመሠረተ አጠያያቂ ያደርገዋል ።

3. ህብረት አንዴ በጋራ ጥረት ከተመሠረተ ያለመው ግብ እስኪደርስ መቀጠል ይኖርበታል ።ግቡን ከመታ ወይም ደግሞ አስፈላጊነቱ ካከተመ በህብረት እንደተመሠረተው ሁሉ በህብረት ማፍረስ አገባብ ያለው አሠራር ነው ። ይሁንና አንዳንድ ድርጅቶች ለግል በሚፈልጉበት መንገድ ህብረቱን ማራመድ ሲሳናቸው ህብረቱ እንዲፈርስ ከህብረቱ ወጣን ሳይሉ ህብረቱ ፈርሷል እያሉ ያስተጋባሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ከህብረቱ ለምን ወጣቹህ ለሚለው ህዝባዊ ጥያቄ የሚረባ መልስ ስለሌላቸው አለንበት ይላሉ ። አንዳንዱማ ግላዊ ፍላጎቱን የሚያረካለት ሌላ ህብረት ሲያይ ግንባር-ቀደም ተሳታፊ በመሆን የመሠረተውን ህብረት በጉባኤ ይፍረስ ሲል ተሰምቷል ። ያ ሳይሳካ ሲቀር ደግሞ ይፍረስ ብሎ በበየነበት ህብረት አለሁ ይላል ።

4. በህብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል መቀራረብና መደጋገፍ ፤ ግልጽና ገንቢ ግንኙነት ፤ በሳልና ትምህርታዊ ውይይት ሲጠበቅ ፤ ቂም በቀልና ጥላቻ የሰፈነበት ፤ የፈሪ ብትር የሆነው ሀሜት የሚወራጭበት ሁኔታ ይታያል ። በጣም አሳፋሪ ሁኔታ !!! ህብረቱ በቅርበት ሲታይ በኢህአዴግ ላይ

ከተነጣጠረው ምት ይልቅ እርስ በርስ ላይ የሚወረወረው ድንጋይ ይበዛል ። መጠላለፍ ይሉታል ይህ ነው ። ድንጋዩ ይብዛ ይከመር የትም እንደማያደርስ እስካሁን መገንዘብአለመቻሉ እጅግ ያሳዝናል ።

5. ልዩነትን የአቋም ይሁን የታሪክ ትንታኔ-ሰበብ በማድረግ ህብረትን የሚገዘግዙ ተግባሮች ተከስተዋል ።

ሀ/ ታሪክ መቸም ያለፈውን እውነታ ማህደር ነው ። በህብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ቦታና ትርጉም የሚሠጠው በጎም ሆነ ክፉ ክንውን ፤ ለመጭው ትውልድ የሚተርፍ ትምህርት ሆኖ መታየት ሲገባው አንዳንዶቹ የቂም በቀል መወጣጫ ፤ ማለትም የፖለቲካ ተቀናቃኝን መምቻ በትር አድርገው ይጠቀሙበታል። ባለፉት 25 ዓመታት ብቻ ብቅ ያሉት ድርጅቶች ታሪክ ስንመለከት ከተጠያቂነት የሚያመልጥ የለም ። ልዩነቱ ግን የጥፋቱ መጠንና ዓይነት እንደሆነና እንደሚሆን የሚያጠራጥር አይሆንም።

ለ/የአቋም ልዩነት አለን ይባላል ። በእርግጥ ደግሞ አለ ። <u>ለምሳሌ</u> በኢትዮጵያ ውስጥ ብሔሮችና ብሔረ-ሰቦች አሉ-የሉም ፤ ወይም ኢህአዴግ በሰላማዊ ትግል ሊወገድ ይችላል-አይችልም — ወዘተ የሚሉ አመለካከቶች ልዩነቶች ናቸው ። ሌሎች ወቅታዊ የልዩነት ርእሶችም ማንሳት ይቻላል ። እነዚህና የመሳሰሉ ልዩነቶች መኖራቸው በስተጀርባ ያዘሉት እኩይ ውጥን እስከሌለ በራሳቸው ክፋት ባልነበራቸው ። እንዲያውም በሳል ውይይት ቢደረግባቸው የያንዳንዱን ወገን ግንዛቤና ንቃት ከፍ እንዲል በረዱ ። ከህሜትና መጯጯህም ተላቀን ትክክለኛውን አቋም ለመያዝም በቻልን ነበር ። እንዲያውም ለሁሉም ወገን እኩል የሆነው የሀገር ህልውና ጉዳይ ፤ የሰዎች ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች መከበር ፤ በታሪክና በሁሉም ተሳትፎ የሚቀረጽ ዘላቂ ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓት የመገንባት ጉዳይ ፤ የሚጠይቀው ህብረት በታሪክና በአቋም ልዩነት ሰበብ ሊደናቀፍ ጭራሽ ባልቻለ ነበር ። በነዚህና በመሳሰሉ ምክንያቶች ህብረቱ የተጠበቀው ለውጥ ሳያስገኝ "አልሞት ባይ ተጋዳይ" ጉዞ ላይ ይገኛል ።

## <u>ከዚህስ ወዴት?</u>

አምባገነኖቹ የኢህአዴግ መሪዎች በኢትዮጵያ ሰላም ያመጣሉ ፤ለዴሞክራሲና ለህዝበ ውሳኔ ተገዢ ይሆናሉ ብሎ የሚያስብ ካለ ፤ ህዝቡንና ራሱን እያታለለ መሆኑ ቀደም ሲል ጠቅሰናል ።እነሱ የቀየሱት የምርጫ ትያትር ለያንዳንዱ ድርጅት የተወሰነ ጠቀሜታ ቢኖረውም ፤ ኢህአዴግ ያልነበረውና የሌለው መልክ አሳምሮ ለማቅረብና ህጋዊ መንግሥት መስሎ ለመቅረብ እንደረዳው አያከራክርም ። በመጭው አምስት ዓመት "ምርጫው" ቢያካሂድም ውጤቱ ያው የአሁኑ ዓይነት ነው ። በተቀናጀ ህዝባዊ አመጽ ካልተያዘ በስተቀር ኢህአዴግ ራሱ በነደፈው ህግም የሚከሰስ ፤ የሚፈረድ እንዳልሆነ ደጋግሞ አረጋግጦታልናል ።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እስካሁን በተከተሉት የትግል ስልት ከቀጠሉ ምንም ዓይነት ለውጥ እንደማያመጡና እንዲያውም ኢህአዴግ በቀደደው ቦይ ገብተው እየተተራመሱ መሆናቸው ቀደም ብለን ለማሳየት ጥረናል ። በዚህ ይዘት ሌላ አሥር ዓመት ቢኬድበትም ለኢህአዴግ ማንሰራራት ይረዳ እንደሆነ እንጂ፤ ለህዝቡም ሆነ ለዴሞክራሲ ኃይሎች እርባና የለውም ። እያንዳንዱ ተቃዋሚ ድርጅት አንዴ ቆም ብሎ ያለፈውን የንትርክና መጠላለፍ አሥር ዓመትና መጭው አሥር ዓመት ቢቃኝ ይበጃል ።

ታዲያ ህብረቱ ለኢህአዴግ ማንሰራራት ምቹ ሁኔታ መፍጠርና የመጠላለፍ አዙሪት ወጥቶ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚፈልገውን ለውጥ ለማምጣት በምን ዓይነት የትግል ዘዴ መጓዝ አለበት? ከላይ የተጠቀሱት ችግሮችስ እንዴት ይወገዳሉ? ችግሮቹ የማይለቁን ከሆኑስ ምንና እንዴት መደረግ አለበት?

ለነዚህ ከባድ ጥያቄዎች መልስ ከመሰንዘራችን በፊት አንድ ግልጽ መሆን ያለበት እውነታ እናስቀምጥ። ይኸውም የአሁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ መከፋፈልና መተራመስ በጥሞና ሲታይ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ አደገኛና አስከፊ ተሪዮ ነው ። አደገኛነቱ በዘመነ- መሳፍንት ከነበረው መከፋፈል እንኳን ይብሳል ። ያኔ ሽማግሌና ሃይማኖት ገላጋዮች ሆነው ማኸል እየገቡ ጠቡን ያበርዱና ህዝቡ ያለ ብዙ ችግር ወደ ሰላማዊ ኑሮ ይመለስ ነበር ። ሲከፋም በአንድ ረፋድ ውጊያ ሰው ይገላገል ነበር ። የወቅቱ ቅራኔ ስፋትና ጥልቀት ግን ከብሔር-ብሔረሰብ ወርዶ ወደ ጎሳ አውራጃና ቀበሌ እንዲሁም በቤተሰባዊ ስብስብ ዓይን ለዓይን የመናቆር ሁኔታ የትም አካባቢ (ትግራይንም ጨምሮ) ይታያል ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ድርጅቶች ብዛት ሲታይ እያንዳንዱ 89 ብሔረሰብ 2 ወይም 3 አንዳንዱም 4 ወይም 5 ድርጅቶች ፈጥረዋል ። ይህ የድርጅት ጋጋታው ሲመረመር ለትርምስና ግጭት የሚያሸጋግር ነው ። ኢህአዴግ ህጋዊ መልክ አስይዞ በቀየሰው ከፋፋይ ስልት ሁሉም እየጋለበ መታየቱ ህዝብና ሀገር የማስቀደሙ አቅጣጫ ምንኛ እንደተሳተና በግል ድርጅት ጥቅም እንደተተካ ሳያሳስበን አልቀረም ።

ከዚህ ገሃድ ሁኔታ ስንነሳና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የተጠናወታቸው የመጠላለፍ በሽታ ስንገነዘብ ህብረቱ ከውስጥም ከውጭም ምንኛ እንደተወጠረ ለመገመት አያዳግትም ። መፍትሔስ አለው ወይ? በርግጥ እንቅፋቱ ይብዛ ይምረር ፤ የአንድ ሀገር ልጆች እስከሆን ድረስ በጋራ የምንቆምላቸው ዓላማዎችና የጋራ ጥቅሞች ስላሉን ህብረቱ ምንጊዜም አስፈላጊ መሆኑ በቅድሚያ ልንደርስበት ይገባል ። ስለሆነም የመቻቻል (compromise)ና የብሔራዊ መግባባት አስፈላጊነት በቅጡ እንድንጨብጠው እየጣርንና የነበሩንን ድክመቶች እያረምን የሚጠበቅብንን በሳል ሃላፊነት ህብረቱን ተግባራዊ በማድረግ መወጣት ይኖርብናል ። ይህን የህብረት ሂደት ተሳክቶ ለማየት ብንበቃም ብቻውን በተለይ ደግሞ አሁን ኢትዮጵያ በምትገኝበት የመከፋፈልና የፖለቲካ ድርጅቶች በመቶዎች የሚቆጠሩበት ደረጃ መድረሱ ሲታይ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የማዋቀሩና በሰላም የዕድገት ጎዳና የመያያዙ ጉዳይ በቀላሉ ተከታትሎ የሚመጣ አይመስልም ። ዋናው ስትራተጂካዊው ጉዳይ ደግሞ ይህንኑ የሰላም የዴሞክራሲና የዕድገት ሂደት ተግባር ላይ ማዋል ነው።

ይህንን ስትራተጂካዊ ጉዳይ እውን ለማድረግ ከህብረት ባሻገር ሊኖር የሚችል የትግል ዘዴና ቅንብሩ ማየት የግድ ይለናል ። ለዚህም ነው የውህደት አስፈላጊነት እንደ ተቀዳሚ ጉዳይ አድርገን ለማቅረብ

የተገደድነው ። እንግዲህ ከህብረት ወዲያ ውህደት ስንል አንድነት የመፍጠር ወይም አንድ ድርጅት የመሆን ቅንብር የሚጋብዝ አማራጭ የምፍትሔው መሳርያ ነው ። በአገር አቀፍ ደረጃ ተመሳሳይ የፖለቲካ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንዛቤዎች በፕሮግራም ደረጃ ያሳፈሩ ድርጅቶች ግለሰባዊ ወይም ግለ ድርጅታዊ ስግብግብነት ካልበከላቸው በስተቀር አንድ ድርጅት የማይሆኑበት ምክንያት አይታየንም ። ተመሳሳይነት ከሌለም እያንዳንዱ ድርጅት አቋሙን ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥ ይኖርበታል ። ውህደት የማይፈልግበት ምክንያት መግለጽ ካልቻለ የሃገር ችግር ለመፍታት የቆምኩ የፖለቲካ ድርጅት ነኝ ማለቱ ማክተም ይኖርበታል ።

ይህ የተሰነዘረው የውህደት መፍትሔ አንድ አወዛጋቢ ጥያቄ ይቀሰቅሳል ። ይኸውም በመለስተኛ ፕሮግራም አብረው በህብረት ሊሠሩ የማይችሉ ድርጅቶች ወደ ውህደት እንዴት ሊሸጋገሩ ይችላሉ? የሚለው ነው ።

ህብረት የተለያየ አመለካከት ያላቸው ድርጅቶች ልዩነታቸውን እንደጠበቁ የሚሰባሰቡበት መድረክ በመሆኑ ተባብረው የሚሰሩበት ብቻ ሳይሆን እርስ በርስም የሚፋተጉበት መድርክ ነው ። በአሁኑ የመከፋፈል "ፋሽን" ሲቃኝ ደግሞ ከሚያስተባብራቸው ይልቅ የሚያጋጫቸው ሁኔታ እያየለ ህብረቱ መዳከሙ ተገንዝበናል። በአንድ የተዋሃደ ድርጅት ግን በአንድ ዓላማና የአሠራር ቅንብር ስለሚተሳሰር ዓላማውና አሰራሩ እስካመነበት ድረስ ሰልፉን ጠብቆ ሊዘልቅ ይችላል ። እንግዲህ ያሁሉ የድርጅት ብዛት በአገር ዓቀፍ ደረጃ መርሆችና ዕቅዶች ሥር መደራጀት ማለትም ውህደት ቢፈጠር ዞሮዞሮ አንድ የግራ ፣ አንድ የቀኝ ፣ አንድ የማኸል ፣ ማለት ሶስት ህብረ ብሔራዊ ድርጅቶች ቢወጣው ነው ። ግፋ ቢልም አንድ የቀኝ አክራሪና አንድ የግራ አክራሪ ቢታከሉበት አምስት አገር ዓቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢኖሩ ነው። በርግጥ አክራሪ ፓርቲ ባይኖር ይመረጣል ። የህዝብ ድጋፍ ይኖረኛል ብሎ ካመነ ግን ህልውናውን የሚጻረር ኃይል መኖር የለበትም ። በዴሞክራሲና - በህዝበ ውሳኔ እስከ ተገዛ ድረስ ችግርም አይኖርም ።

ለኢህአዴግ አመቺ ዒላማ በመሆን ተበታትነው ያሉ ትናንሽ ድርጅቶች (በስም ብቻ ወይም በግርግር ትልቅ አይኮንምና) ውህደት ቢፈጥሩ ግን የዓላማና የግብ አንድነት ከመመሥረት ባሻገር ገንቢ ሃሳብ ፣ ጉልበት ፣ ገንዘብ ፣ ደጋፊ - ወዘተ በአንድ አቅጣጫ ስለሚቀናጅ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ይሁን የሚመታው ግብ ፍሬያማ ይሆናል ። በህብረት ትግል ሊከፈል ወይም ሊጠየቅ የሚያዳግተው መስዋዕትነት ፣ በውህደቱ ግን በቀላሉ ሊገኝ ይችላል ።

አሁን አገራችን ኢትዮጵያ ያለችበት የመከፋፈል አደጋ ሲታይና በዚሁ ከቀጠለም ነገ ሊፈጠር የሚችል ደም - ለበስ ትርምስ ስናሰላስል ያለብንን የግለሰብ ይሁን የድርጅት ስግብግባዊ ፍቅር ወዲያ ጥለን, ትንሽ, ትልቅ ድርጅት ሳንባባል ለሀገራችን ህልውናና ለህዝባችን ደህንነት ስንል መርሆአዊ ውህደት ፈጥረን ከፋፋዩ ኢህአዴግን መታገል የግድ ይለናል ። በተዋሀደ ትግል የማይደረመስ ጨቋኝ ሥርዓት አይኖርም ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባትም ከባድ አይሆንም ።

ለዚህም ነው ት.ዴ.ት ትብብር የሚል ስም አንግቦ በህብረቶቹ ሂደት ፀንቶ እየተሳተፈ የውህደት ውይይት እንዲከፈት ደጋግሞ የወተወትው ። በቅርቡም ኅዳር 2000 ዓ.ም.ፈ በቶሮንቶ ባካሄደው ጉባኤ ዋናው ርእስ አድርጎ በመውሰድ ፣ የውሂደት ውይይት ተብሎ ይጀመር ዘንድ ከህብረት ወደ ውህደት እንሸጋገር ሲል ጥሪ ያቀረበው ። አሁን ያሉት ህብረቶች - ኢተፖድህን ጨምሮ - ይህን የውህደት ጥሪ ተቀብለው ተግባር ላይ የሚውልበት እርምጃ እንዲወስዱ ይጠይቃል ። ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉም የህብረቱ ይሁን የውህደቱ ሂደት ተሳክቶ ሃገራችን ካለችበት የመከራ ዓዘቅት ትወጣ ዘንድ ጥግ ይዞ "ምን እየሠራቹህ ነው?" ከማለት ፣ በአንድ በኩል ድጋፍ እየሰጡ በሌላ በኩል ህብረቱንና ውህደቱን የሚያደናቅፉትን እየተከታተለ በማረም ንቁ ዜግነታዊ ተሳትፎ እንዲያሳዩ ያሳስባል ።

አምባገነኖች እና አስመሳዮች ይወድቃሉ !

ተዋህደን አገራችንና ህዝባችንን እናድን ።

ት.ዴ.ት ጥር 2001 ዓ.ም.ፈ